# ዌስት ናይል ቫይረስ

DCHHS
Safe families, healthy lives.
Dallas County Health and Human Services

***ዌስት ናይል ቫይረስ ምንድነው?*** ዌስት ናይል ቫይረስ (WNV) ታሪካዊ መገኛው በአፍሪካ፣ ምእራብ ኤዥያ እና መካከለኛ ምስራቅ አከባቢዎች ላይ የሆነ ፌላቪቫይረስ ነው። በትንኝ ከሚተላለፉ የቫይረስ ቡድኖች ውስጥ አንዱ ነው። ይህ ቫይረስ ሰዎችን፣ አእዋፋትን፣ ትንኞችን፣ ፈረሶችንና ሌሎች እንስሳቶችን ሊያጠቃ ይችላል። WNV ከተራ እስከ አደገኛ በሽታ ሊያስከትል ይችላል። አብዛኛዎቹ በዚህ ቫይረስ የሚያዙ ሰዎች አይታመሙም። አንዳንዶች ደግሞ ጉንፋን መሰል በሽታ ይይዛቸዋል። አልፎ አልፎ ደግሞ ቫይረሱ አንጎልና አከርካሪን በማጥቃት የአንጎል መቃጠል በማስከተል አደገኛ ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል። WNV ያጋጥመኝ ይሆን ብሎ ፍርሀት ውስጥ መግባት አስፈላጊ ባይሆንም ጉዳዩን አስቀድሞ ማወቅ ግን አስፈላጊ ነው። ቫይረሱን እና ኢንፌክሽኑ የምንከላከልባቸው መንገዶችን የተመለከተ እውቀት መጨበጥ ወሳኝ ነው። የሚወስዷቸው ጥንቃቄዎች እንዲሁም ከሌሎች በወባ ትንኝ የሚመጡ በሽታዎችም ይከላከልልዎታል።

***WNV የሚሰፋፋባቸው መንገዶች ምንድናቸው?*** በአጠቃላይ በWNV የተለከፈ ትንኝ አንድን ሰው በሚነክስበት ጊዜ ይተላፋል። ትንኞች በWNV የተጠቁ አእዋፋት በሚነክሱበት ጊዜ ይለከፋሉ። የተለከፉ ትንኞች ሰዎችን ወይም እንስሳትን በመንከስ WNV ያስፋፋሉ። WNV ቫይረሱ ካለው ሰው ጋር በመገናኘት፣ በመነካካት ወይም በመሳሳም አይተላለፍም። በእጅግ ጥቂት አጋጣሚዎች ደግሞ WNV በደም ልውውጥ ጊዜ፣ የአካል ንቅለተከላ ጊዜ፣ ጡት በማጥባት እንዲሁም በእርግዝና ጊዜ ከእናት ወደ ህጻን ሊተላለፍ ይችላል።

***የ WNV ምልክቶች ምንድናቸው?*** አንድ ሰው በተለከፈ ትንኝ ከተነከሰ በኋላ ከ 3 እስከ 14 ቀናቶች ውስጥ ምልክቶች ይታዩበታል። WNV ማእከላዊ ስርአተ ነርቭን ሊያጠቃ ይችላል። የምልክቶች ክብደት ከሰው ወደ ሰው ሊለያይ ይችላል።

- **አብዛኞቹ ሰዎች ምልክት አይታይባቸውም።** ወደ 80% የሚሆኑ በWNV የተጠቁ ሰዎች ምንም አይነት ምልክት ካለማሳየታቸውም በላይ በቫይረሱ መጠቃታቸው አያውቁም።
- **በተወሰኑ ሰዎች ደግሞ ቀላል ኢንፌክሽን ይታይባቸዋል።** ወደ 20% የሚሆኑት በበሽታው የተጠቁ ሰዎች ቀላል ጉንፋን መሰል ምልክቶች፣ ራስ ምታት እና የሰውነት ህመም፣ ማቅለሽለሽ፣ ማስታወክ፣ የጣፍያ ግድግዳ እብጠት፣ እንዲሁም በደረት፣ ሆድ፣ ጀርባ ላይ የሚወጣ ሽፍታ የመሳሰሉ ምልክቶች ይታዩባቸዋል። ምልክቶች ለተወሰኑ ቀናት ሊቆዩ ይችላሉ። ይህ የዌስት ናይል ትኩሳት በመባል ይታወቃል።
- **በተወሰኑ ሰዎች ከባድ ኢንፌክሽን ያስከትላል።** በWNV ከተጠቁ 150 ሰዎች ውስጥ አንዱ እንደ ዌስት ናይል ኢንሰፋሊቲስ፣ ዌስት ናይል ሜኒንጊትስ፣ ወይም ዌስት ናይል ሜኒንጎኧንሴፋሊትስ ለመሳሰሉ ከባድ በሽታዎች ሊጋለጥ ይችላል። ራስ ምታት፣ የአንገት ድርቀት፣ ግራ መጋባት እንዲሁም ከፍተኛ ትኩሳት ከምልክቶቹ ውስጥ ይገኙበታል። እነዚህ ምልክቶች ለብዙ ሳምንታት ወይም ወራቶች ሊዘልቁ ይችላሉ። ቋሚ የሆነ ኒዩሮሎጂካዊ ችግር ትተው ሊያልፉ ይችላሉ።
- **WNV በጣም አልፎ አልፎም ቢሆን ሞትን ሊያስከትል ይችላል።**

***WNV እንዴት ነው የሚታከመው?*** ለWNV ኢንፌክሽን የተወሰነ ህክምና የለውም። በቀላል ኢንፌክሽን ጊዜ ሰዎች በራሳቸው ጊዜ የሚከስሙ እንደ ትኩሳት እና ህመሞች የመሳሰሉ ምልክቶች ያጋጥመዋቸዋል። በሽታው ከባድ በሚሆንበት ጊዜ ሰዎች ወደ ሆስፒታል በመሄድ እንደ ፈሳሽ በትቦ የመውሰድ፣ የመተንፈስና የነርሲንግ እንክብካቤ የመሳሰሉ ድጋፍ ሰጪ ህክምናዎች ማግኘት ሊኖርባቸው ይችላል።

***WNV ይዞኛል ብየ በምጠራጠርበት ጊዜ ማድረግ ያለብኝ ምንድነው?*** WNV ይዞኛል ብለው የሚጠራጠሩ ከሆነ በአስቸኳይ በዶክተርዎ ወይም የጤና እንክብካቤ ሰጪዎ መታየት ይኖርብዎታል። በሽታዎን ለማወቅና ለማከም የሚያስችሉ ምርመራዎችን ያደርጉልዎታል። ቀላል የWNV በሽታ በአብዛኛው ጊዜ በራሱ ጊዜ ይተዋል። ከባዱ የWNV በሽታ አይነት ከያዝዎና እንደ ከባድ ራስምታት ወይም ግራ መጋባት ያሉ ምልክቶች ከታዩብዎ በፍጥነት ወደ ህክምና ይሂዱ።

***ምን ማድረግ አለብኝ?*** **በ4D አማካኝነት ይከላከሉ።**

- ***ቆዳዎን በየቀኑ ቀኑን ሙሉ ጸረ ትንኝ ቅባት ይቀቡት***
  ከቤት ውጪ በሚሆኑበት ጊዜ የዲት ይዘት ያላቸው ጸረ ትንኝ ቅባት ወይም ሌላ በEPA የጸደቁ የጸረ ትንኝ ቅባቶች በመመሪያ መሰረት ይጠቀሙ።
- ***ይልበሱ***
  ረዥም፣ ቀለል ያለ እና ቀላል ቀለም ያለው ልብስ ይልበሱ።
- ***ፈሳሽ ማድረቅ***
  እቤት ውስጥም ከቤት ውጪም ያለ ማንኛውም ያቆረ ውሃ ያስወግዱ።
- ***ማታ & ጠዋት***
  ማታና ጠዋት ትንኞች በብዛት የሚንቀሳቀሱበት ጊዜ በመሆኑ በተቻለ መጠን ከቤት አይውጡ።